መልእክት አሥራ አንድ

## ክህደት፣ የኮረብታ መስገጃዎች
## እና የእውነተኛው የአንድነት መቆሚያ ስፍራ ምለሳ

የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ፡- 1 ነገ. 12፡25-33፤ 13፡33-34፤ ዘዳ. 12፡2-18

**I. የኢዮርብዓም ክህደት የዛሬው ክርስትና ምሳሌ ተደርጎ መቆጠር ይችላል— 1 ነገ. 12፡25-33፤ 13፡33-34፡-**

ሀ. ክህደት ማለት የእግዚአብሔርን መንገድ መተው እና ከእግዚአብሔር ውጪ ሌሎች ነገሮችን ለመከተል በሌላ መንገድ መሄድ እና በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እና እግዚአብሔርን በማምለክ ካባ ነገሮችን ለራስ ማድረግ ነው—ሐዋ 9፡2፤ 18፡26፤ 2 ጴጥ. 2፡2፣ 15፣ 21፤ ይሁ. 11፤ መሳ. 18፡30-31።

ለ. የኢዮርብዓም ክህደት አምስት ነገሮችን ይዟል፡-

1. ኢዮርብዓም ሕዝቡን በኢየሩሳሌም ከማምለክ ለማዘናጋት ሁለት የወርቅ ጥጆችን (ጣዖታትን) ሠራ፣ አንዱን በቤቴል ሌላኛውን በዳን አስቀመጠ፣ በዚህም የእስራኤልን ልጆች አንድነት ለመጠበቅ በቅድስቲቱ ምድር ላይ ልዩና ብቸኛ የማምለኪያ ማዕከል እንዲኖር የሚለውን የእግዚአብሔርን ድንጋጌ ጣሰ—1 ነገ. 12፡26-30፤ ዘዳ. 12፡2-18።
2. ኢዮርብዓም በኮረብታማ ስፍራዎቹ ላይ መቅደስን ገነባ፣ ከሌዊ ነገድ ያልሆኑ ካህናትን ከተራው ሕዝብ መካከል ካህናት አድርጎ ሾመ—1 ነገ. 12፡31፤ 13፡33፤ 2 ዜና. 13፡9።
3. ኢዮርብዓም በስምንተኛው ወር በአሥራ አምስተኛው ቀን (በልቡ ባሰበው ወር) በይሁዳ እንደሚደረግ በኣል ያለ በኣል እንዲደረግ ወሰነ—1 ነገ. 12፡32፣ 33።
4. ኢዮርብዓም በቤቴል ባለው መሠዊያ ላይ ለቀረፃቸው ጥጆች መሥዋዕትን ሰዋ፣ የኮረብታ መስገጃዎቹንም ካህናት በቤቴል አስቀመጠ—ቁ. 32-33።
5. ኢዮርብዓም ካህን ባይሆንም ወደ መሠዊያው ወጣ—ቁ. 33።

ሐ. የኢዮርብዓም ክህደት መላው ቤተሰቡ ከእግዚአብሔር ፍርድ በታች እንዲጠፉ እና ኋላም እስራኤል ወደ ምርኮ እንዲጋዙ ያደረገ ከባድ ኃጢአት ሆነ—13፡34፤ 14፡7-11፤ 15-16፤ 15፡29-30፤ 2 ነገ. 17፡20-23።

መ. በዛሬዎቹ "ኢዮርብዓሞች" የተመሠረቱት የአምልኮ ማዕከላት በእርግጥ የራስን ምኞት የማሳካት ማዕከላት ናቸው፡-

1. በክርስትና ውስጥ ያሉት ክፍፍሎች ከራስ ወዳድነት እና የራስን ምኞት ከማሳካት የመጡ ናቸው።
2. አንዳንዶች የራሳቸውን ስግብግብ ፍላጎት ለማርካት የራሳቸውን ግዛት ያገኙ ዘንድ ከፍተኛ ጉጉት ስላላቸው የእግዚአብሔርን ምርጫ ቸል ይላሉ።

ሠ. በእግዚአብሔር አዲስ ኪዳን ኢኮኖሚ ሁሉም የእውነት በክርስቶስ የሚያምኑ አማኞች ሁሉ ለእግዚአብሔር ካህናት ተደርገዋል፣ የዘቀጠው ክርስትና ግን አንዳንዶችን በሥልጣን ተዋረድ ተሿሚ አገልጋዮች በማድረግ እና ቀሪዎቹን አማኞች እንደ ተገልጋዮች በመተው፣ አንዳንድ አማኞች የእግዚአብሔርን አገልግሎት እንዲሠሩ ለመሾም ሥርዓትን ገንብቷል፤ ይህ ልንፀየፈው እና ልናስወግደው የሚገባ የክህደት ልምምድ ነው—1 ጴጥ. 2፡9፣ ራእ. 1፡6፤ 5፡10፤ 2፡6፣ 15።

ረ. የዛሬው ክርስትና በክህደት የተሞላ ስለሆነ፣ ጌታ ምለሳን—የሕይወትን እና የእውነትን ምለሳ—ይፈልጋል—ኤር. 2፡11፣ 13፣ 19፤ ራእ. 2፡6፣ 15፤ 1 ዮሐ. 1፡1-2፣ 5-6፤ ዮሐ. 18፡37፤ 10፡10።

ሰ. የሕይወት አቅርቦት እና የእውነት መገለጥ ሐዋርያት ክህደትን እና የቤተ ክርስቲያንን ዝቅጠት ሲዋጉ የተጠቀሙአቸው ማርከሻዎች ናቸው— 1 ዮሐ. 1፡1-2፣ 5-6፤ ዮሐ. 18፡37፤ 10፡10፤ 2 ጴጥ. 1፡3-21፤ 2 ጢሞ. 1፡1፣ 10፤ 2፡15፣ 25።

**II. ለእውነተኛው፣ ሁሉን-ላካተተው አንድነት ምለሳ እና መጠበቅ፣ የኮረብታ መስገጃዎችን ማጥፋት አለብን— 1 ነገ. 11፡7-8፤ 12፡26-33፤ 13፡33-34፤ 14፡22-23፤ 15፡14፤ 22፡43፤ 2 ነገ. 12፡2-3፤ 14፡3-4፤ 15፡3-4፣ 34-35፡-**

ሀ. የኮረብታ መስገጃዎች አሕዛብ አማልክቶቻቸውን የሚያመልኩባቸው ስፍራዎች ነበሩ።

ለ. የእስራኤል ልጆች የከነዓንን ምድር ለመውረስ ወደ ከንዓን ሲገቡ፣ እግዚአብሔር የአሕዛብን የኮረብታ መስገጃዎች ሁሉ እንዲያጠፉ አዘዛቸው—ዘዳ. 12፡1-3፡-

1. የኮረብታ መስገጃዎችን ማቆም ክፍፍል እንዲኖር ማድረግ ነው፤ ስለዚህም፣ የኮረብታ መስገጃዎች ትርጉም ክፍፍል ነው።

2. የሕዝቡን አንድነት ለመጠበቅ እግዚአብሔር [ሕዝቡ] የእርሱ ምርጫ ወደ ሆነው ልዩና ብቸኛ ስፍራ እንዲመጡ ይፈልግ ነበር፤ የኮረብታ መስገጃዎቹ የዚህ ልዩና ብቸኛ ስፍራ ምትኮች እና አማራጮች ነበሩ—ቁ. 8፣ 11፣ 13-14፣ 18።
3. በ 1ኛ ነገሥት፣ ሁለት ነገሥታት—ሰሎሞን እና ኢዮርብዓም—የቀደመው የሥጋ ምኞቱን ለማርካት ከመፈለግ የተነሣ፣ ኋለኛው አንደኛ የራስ ምኞቱን ለማሳካት ከመፈለግ የተነሣ፣ የኮረብታ መስገጃዎችን ለማቆም ቅድሚያውን ወሰዱ—11:7-8፤ 12:27።

ሐ. የኮረብታ መስገጃ ከፍታ፣ መደበኛ ከሆነው ደረጃ ከፍ ያለ ነገር ነው፦
1. ይህ የሚያመለክተው የኮረብታ መስገጃ የአንድን ነገር ከፍ ከፍ መደረግ እንደሚያካትት ነው።
2. በመርህ ደረጃ፣ በክርስትና ውስጥ ያለ እያንዳንዱ የኮረብታ መስገጃ፣ እያንዳንዱ ክፍፍል ከክርስቶስ ውጪ ሌላን ነገር ከፍ ከፍ ማድረግን ያካትታል—ተዛ. ቆላ. 1:18።

መ. በሰሎሞን እና በኢዮርብዓም የተደረገው የኮረብታ መስገጃዎች ግንባታ ዘገባ መንፈሳዊ ትርጉም አለው፤ የተጻፈውም ለመንፈሳዊ ትምህርታችን ነው—ሮሜ 15:4-6፦
1. በሰሎሞን እና በኢዮርብዓም የተገነቡት የኮረብታ መስገጃዎች የአንድነትን የመቆሚያ ስፍራ ክፉኛ ጎድተዋል—1 ነገ. 11:7-8፤ 12:26-33።
2. በቤተ ክርስቲያን ሕይወት ውስጥ ምንም አይነት የኮረብታ የመስገጃዎች ሊኖሩን አይገባም፤ በምትኩ ክርስቶስን ከፍ ከፍ ለማድረግ ሁላችንም በተመሳሳይ ደረጃ ላይ ልንሆን ይገባል—ቆላ. 1:18፤ 3:10-11።
3. የትኛውም የኮረብታ መስገጃ፣ እውነተኛ መሥዋዕቶች የሚቀርብባቸው እንኳን፣ የአንድነት የመቆሚያ ስፍራ ላይ ጉዳት ያደርሳል።

ሠ. የኮረብታ መስገጃዎች መጥፋት ሦስት ዋና ነገሮችን ያካትታል፦ ስፍራዎቹን፣ ምስሎቹን እና ስሞቹን—ዘዳ. 12:2-3፦
1. በመንፈሳዊ አነጋገር፣ ከቤተ ክርስቲያን ውጪ የሆነን እያንዳንዱን ስፍራ እና ከክርስቶስ ስም ውጪ የሆነን እያንዳንዱን ስም ማጥፋት አለብን፤ ይህ ማለት ባህላችንን፣ ልዩ ጠባያችንን፣ ባሕሪያችንን፣ ልማዶቻችንን፣ ተፈጥሮአዊ መገለጫዎቻችንን፣ ምርጫዎቻችንን፣ ኃይማኖታዊ የኋላ ታሪካችን ከነተፅእኖው—እውነተኛውን አንድነት የሚያጠፋ ነገርን ሁሉ—ማስወገድ አለብን—ገላ. 2:20፤ 5:24፤ 6:14።
2. በቆላስይስ 3:11 ላይ ያለውን ቃል ለመፈጸም፣ እያንዳንዱ ሌላ ስፍራ ፈጽሞ መጥፋት አለበት፦
   ሀ. ክርስቶስ ያላት ቤተ ክርስቲያን ያልሆነን ነገር ሁሉ ማጥፋት አለብን።
   ለ. እንደ መልካሚቱ ምድር ብልጥግናዎች ክርስቶስን በመደሰት በቤተ ክርስቲያን ሕይወት ውስጥ መሆን አለብን—ዘዳ. 8:7-9፤ ኤፌ. 3:8።
3. የኮረብታ መስገጃዎቹን ለማጥፋት ፈቃደኝነት ከማጣት የተነሣ የቤተ ክርስቲን ሕይወት ተዳክሟል—1 ነገ. 15:14፤ 22:43፦
   ሀ. በስብዕና ሕይወታችን እና ባህላችን ውስጥ መጥፋት የሚያስፈልጋቸው አሁንም ድረስ ያሉ ብዙ ስፍራዎች አሉ፤ ሁሉንም ማጥፋት እና እግዚአብሔር ወደ መረጠው ልዩና ብቸኛ ስፍራ፣ ወደ ቤተ ክርስቲያን መሄድ አለብን—ገላ. 5:24፤ ማቴ. 16:18።
   ለ. መጥፋት ባለበት እያንዳንዱ ስፍራ፣ መታሰቢያ የሆነ ዓምድ፣ ምልክት ወይም ምስል አለ፤ በባሕርያችን ወይም በልዩ ጠባያችን ውስጥ መጥፋት የሚገባቸው እንዲህ ያሉ አዕማድ፣ ምልክቶች ወይም ምስሎች ሊኖሩ ይችላሉ።
   ሐ. በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ከክርስቶስ ውጪ ሌላ ነገር መኖር አይችልም፤ ክርስቶስ ሁሉን እና በሁሉ ውስጥ መሆን አለበት—ቆላ. 1:18፣ 27፤ 2:2፤ 3:11።

**III. በመላው ክርስትና ዓለም ውስጥ ካለው ክህደት፣ የኮረብታ መስገጃዎች እና ክፍፍሎች የተነሣ፣ የእውነተኛው የአንድነት መቆሚያ ስፍራ ምለሳ አስፈላጊነት አለ—ኤፌ. 4:2-6፣ 13፤ ዮሐ. 17:11፣ 14-23፤ 1 ቆሮ. 10:16-17፦**

ሀ. በአዲስ ኪዳን ባለው መለኮታዊ መገለጥ መሠረት፣ የቤተ ክርስቲያን የመቆሚያ ስፍራ—እውነተኛው የአንድነት የመቆሚያ ስፍራ—ከሦስት እጅግ አስፈላጊ ከሆኑ ንጥረ-ነገሮች የተዋቀረ ነው፦
1. የመጀመሪያው የቤተ ክርስቲያን መቆሚያ ስፍራ አዋቃሪ ንጥረ-ነገር የአጽናፍ-ዓለማዊው የክርስቶስ አካል ልዩና-ብቸኛ አንድነት ነው—ኤፌ. 4:4፦
   ሀ. ይህ አንድነት “የመንፈስ አንድነት” ተብሎ ይጠራል—ቁ. 3።

ለ. ይህ አንድነት ጌታ በዮሐንስ 17 ላይ የጸለየለት አንድነት ነው—በሂደት ያለፈው ሦስታንዱ አምላክ በክርስቶስ ከሚያምኑ አማኞች ሁሉ ጋር በመዋሐዱ የሆነ አንድነት— ቁ. 6፣ 11፣ 14-24።

ሐ. ይህ አንድነት በክርስቶስ በሕይወት መንፈስ ዳግም ሲወለዱ በክርስቶስ ወደሚያምኑ አማኞች ሁሉ መንፈስ ውስጥ እንደ መለኮታዊው ሕይወት ተጨምሯል።

2. ሁለተኛው የቤተ ክርስቲያን መቆሚያ ስፍራ ንጥረ-ነገር አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን የምትመሠረትበት እና የምትኖርበት ልዩና ብቸኛው የአጥቢያ መቆሚያ ስፍራ ነው—ሐዋ. 14፡23፤ ቲቶ 1፡5፤ ራእ. 1፡11።

3. የቤተ ክርስቲያን መቆሚያ ስፍራ ሦስተኛው ንጥረ-ነገር በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ልዩና-ብቸኛ መቆሚያ ስፍራ ላይ የአጽናፍ-ዓለማዊውን የክርስቶስን አካል ልዩና-ብቸኛ አንድነት የሚገልጠው የመንፈስ አንድነት እውነታ ነው—1 ዮሐ. 5፡6፤ ዮሐ. 16፡13፦

ሀ. የመለኮታዊው ሥላሴ ሕያው እውነታ በሆነው በእውነታ መንፈስ፣ የክርስቶስ አካል አንድነት እውን እና ሕያው ይሆናል።

ለ. በዚህ መንፈስ በኩል የቤተ ክርስቲያን መቆሚያ ስፍራ በሕጋዊነት ሳይሆን በሕይወት ይተገበራል።

ሐ. በዚህ መንፈስ እውነተኛው የቤተ ክርስቲያን መቆሚያ ስፍራ ከሦስታንዱ አምላክ ጋር ተገናኝቷል—ኤፌ. 4፡3-6።

ለ. ቤተ ክርስቲያን፣ ሕይወታዊዋ የክርስቶስ አካል ያልተከፋፈለች እና ልትከፋፈል የማትችል ናት፤ ይህች ልዩና ብቸኛ አካል ልክ በሦስታንዱ አምላክ እንዳለው በመለኮታዊው አንድነት እና በመለኮታዊው ባሕርይ፣ ንጥረ-ነገር፣ ውስጠ-ነገር፣ መገለጥ፣ አገልግሎት እና ምስክርነት በብዙ አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት ትገለጣለች— ራእ. 1፡11፤ ዮሐ. 17፡11፣ 21፣ 23።

ሐ. እውነተኛው አንድነት—በእግዚአብሔር ባሕሪ መሠረት የሆነው አንድነት—አዎንታዊ ነገሮችን ሁሉ የሚያካትት ሁሉን-ያካተተ፣ ሁሉን አቀፍ አንድነት ነው—መዝ. 23፡6፤ 36፡8-9፤ 43፡3-4፤ 84፡1-8፣ 10-12፤ 92፡10፤ 133፡1፣ 3፦

1. አንድነቱ ሲመለስ፣ ሁሉም መንፈሳዊ ብልጥግናዎች እና ሁሉም አዎንታዊ ነገሮች አብረውት ይመለሳሉ፣ ምክንያቱም እነዚህ ሁሉ ሕልውና ያላቸው በአንድነት ውስጥ ነውና— ኤፌ. 4፡3፤ 3፡8።

2. እግዚአብሔርን ለመምሰል የሚሆኑ ነገሮች ሁሉ እና መንፈሳዊ ብልጥግናዎች ሁሉ የእኛ የሚሆኑት በእውነተኛው የአንድነት መቆሚያ ስፍራ ላይ ነው—ዘዳ. 8፡7-9፤ 12፡12፣ 26፡28።

3. እውነተኛው አንድነት ከፊል አንድነት አይደለም፤ ታላቅ፣ ሙሉ፣ ሁሉን አቀፍ አንድነት ፣ በሙላት የሆነ አንድነት ነው—መዝ. 133፡1፦

ሀ. ይህ አንድነት፣ በኤፌሶን 4፡3-6 እንደተገለጠው፣ እግዚአብሔር አብን፣ ክርስቶስ ጌታን እና እንደ ሕይወት ሰጪ መንፈስን ያካትታል።

ለ. ሁሉን-ያካተተው አንድነት ወደ ሁሉም አዎንታዊ [የስብዕና] ሰናይ-ባሕርያት እና [የመለኮት] ባሕርያት መግባትን ይሰጠናል—ቁ. 1-2።

መ. ስለ የኮረብታ መስገጃዎቹ መጥፋት እና ስለ እውነተኛው፣ ሁሉን-ያካተተ አንድነት ምለሳ እና መጠበቅ ራእይ ጌታን እናመሰግነዋለን፣ እናወድሰዋለንም፤ ዛሬ በጌታ ምለሳ ውስጥ ይህን አንድነት ማወቅ፣ መለማመድ እና መደሰት ልዩ መብታችን ነው—መዝ. 133፡1፣ 3፤ ዮሐ. 17፡21-23፤ ኤፌ. 4፡3-6።

© 2022 Living Stream Ministry